# ዲያብሎስን ተቃወሙት!!![1]

ወንድሙ መኰንን

ምን ይሰማ ጆሮ፣ ምን ይውጥ ጉሮሮ
ዲያብሎስ አመሰን፣ ጉድ ፈላ ዘርንድሮ።
ዲያብሎስ አምልጦ፣ ከገሀነም ከወጣ
በአሜሪካ አቋርጦ፣ ኢትዮጵያ ከመጣ
ሀይማኖት አዋርዶ፣ አስታቀፈን ጣጣ
የጣጣ መንጣጣት!
መንኰሴውን አርዶ፣ ደማችውን ጠጣት።
እንደ ሼኽ አላሙዲ፣ አክሴማው የነጣ
ጀለቢያ አጥልቆ፣ ቤተ-መቅደስ መጣ።
ሼኹማ ምን አለ፣ በዕምነቱ ያመነ፣
ዲያብሎስ ነው ኢንጂ፣ ሳይበቃ የመነነ።
መስቀል በጁ ይዞ፣ ሹኅጡን ሰውሯል
በንዋየ ፍቅር፣ ልቦናው ታውሯል።
ስድስት ስድሳ-ስድስት መለያውን አውልቆ
መታወቂያ ቁጥሩን፣ ቆቡ ስር ደበቆ
ባሕታዊው ቀበሮ፣ በጎች መሀል ዘልቆ
እረኛ ነኝ አለ፣ ትኰላ ለምድ አጥልቆ።
ይገርማል፣ ይደንቃል፣
ከክፋት ባሻገር፣ ተንኰሉ ይልቃል።
ንዋየ-ቅዱሳትን፣ በዝብዞ የዘረፈ
ያ ነጣቂ ተኩላ፣ መንኰሶት አረፈ።
ታቦቷን ሊሰርቃት፣ ቤተክሲያን አምሶ
ሳይበቃ መንኖ፣ አረፋት መንኰሶ።
በስመ አብ-በስመ አብ! አልኩኝ ሰይጣኑን ፈርቼ፣
ጋነኑ ሲጸጽስ፣ ሲነግስ አይቼ።
ከሲዖል ኮብላዩ፣ እየገሠገሠ።
ስንቱን አሰናከሎ፣ ጳጵሶ ነገሠ።
የተንኰሉ ጽዋ፣ ሞልቶ አልፎ ተረፈ፣
መጻጻሱ ሲገርም፣ ፐትርኮት አረፈ።
ነግሬአችሁ ነበር፣ ግጥም አስመስዬ፣
ዲያብሎስ ሰይጣን እንጂ፣ ካህን አይደለም ብዬ፣
ሹክ ብዬ ነበር፣ በብዕር ተከልዬ፣
ተኰላ ነጣቂ እንጂ፣ መሪ አይሆንም ብዬ
አስመሳዩ መሲህ፣ ቀጣፊ ነው ብዬ።
የሲዖሉ ከይሲ፣ ቀሳፊ ነው ብዬ።[2]
ጳጳሳት ቆጶሳት፣ አባቶች ካህናት
መቅደስ አገልጋዮች፣ ወንድሞች ዲያቆናት
አንድ አምላክ አማኞች፣ ምዕምናን ምዕምናት
ከናንተ ባላውቅም፣ ምክሬን አድምጧት
ሥጋችሁ ቢወገር፣ ነብሳችሁን አድኗት።
የሚሰማኝ ጠፍቶ፣ ስጮህ እስከዛሬ፣
ሊውጣን ያጓራል፣ ዲያብሎስ ክፉ አውሬ።
መቅደሱን አርክሶ፣ ድፍረቱ ጥፋቱ
የዲያብሎስ ሸንገላ፣ ተንኰሉ፣ ክፋቱ!

---

[1] ያዕቆብ ፬፣ ቁ ፯-፰

ብጹአን ሲኖዶስ፣ የእግዚአብሔር ሠራዊት
ትግላችሁ መሪር ነው፣ ከእርኩሳን አራዊት
ሸከማችሁ ቢከብደም፣ ቢያከልም ተራራ፣
ውጦ ሊሰለቅጥ፣ ዲያብሎስ ቢያጓራ
ሊጨፈጭፋችሁ፣ ጭፍራ ቢያሰማራ
በዕምነታችሁ ጽኑ፣ ዕውነት እንድትበራ፤
ሙሴ ቢከዳችሁ፣ ልባችሁ እንዳይፈራ፣
ገብርዔል ቢርቃችሁ፣ ሚካዔል ይጠራ።
ዘዴ ቢቀይስም፣ በተንኰል በመላ
እንዳትጠመዱ፣ በዲያብሎስ ሸንገላ።
እስቲ እግዚዖ በሉ፣ ምሕላችው ይሰማ።
ችላ ያለው አምላክ፣ ምናልባት ቢሰማ።
የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር፣ ወስዳችሁ ልበሱ
በዲያብሎስ ዘመቻ፣ ሳትደመሰሱ።
ፍልሚያው ተጧጡፏል፣ ጦርነቱ ከባድ፣
በዲያብሎስ ድንፋታ፣ እምነታችን አይናድ!
ከዲያብሎስ ውሪዎች፣ ከአለቆች ሥልጣናት
ከአፋሽ ከአጎንባሹ፣ ከካዳሚ ነፍሳት፣
ደም ሥጋ ካልለበሱ፣ መናፍስት ሰይጣናት።
የዲያብሎስ ጭፍራ፣ የጨላማ ገዦች፣
እርኩሳን አጋንንት፣ አፍዝ አደንዛዦች።
ጦር ሜዳ ላይ ናችሁ፣ ጸልዩና ጹሙ፣
እንዳታንቀላፉ ነቅታችሁ፣ ዘብ ቁሙ፤
በዲያብሎስ ተንኰል እንዳትቀደሙ፤
በሰላሙ ወንጌል፣ እግራችሁን ተጫሙ።
የዲያብሎስ ወከባ፣ ቢያስደነግጥ ከቶ
ወገባችሁን ጠበቅ፣ በዕምነትን ቀበቶ
ተጠቃን ብላቻሁ፣ እንዳትናደዱ!
የመንፈስ ቅዱስ እሳት፣ቦግ አድርጋችሁ አንድዱ
ወደ ፈጣሪአችሁ በአንድነት ስገዱ
ዲይብሎስን አስራችሁ፣ ወደ ሲዖል ንዱ።
ሊፈጀችሁ መጣ፣ የዲባሎስ ሐሩር
ኣጥልቃችሁ ቁሙ፣ የመጽደቅ ጦር ጥሩር
ምዕምናን ተነሱ፣ የዕምነት ጋሻን አንሱ
በዲያብሎስ ሠራዊት፣ ሳትገረሰሱ።
የመዳን ቁር ድፉ፣ የመንፈስ ሰይፍ ያዙ
እግዚአብሐር ቃል ሳንጃ፣ ዕምነትን ምዘዙ።[3]
የዲያብሎስ ተንኰል ድር፣ እንድትበጣጥሱ!
"ኤሎሄ! ኤሎሄ!" ብላችሁ ተነሱ!!
ፍቅርን ተላበሱ፣[4]፣ ፍቅር ያሸንፋል፣
ተቃወሙት ዲያብሎስን ፣ ከናንተም ይሸሻል።

**ማሳሰቢያ፡** ይኸ ግጥም ልቦለድ የሆነ የኪነጥበብ ውጤት ነው። በዝህ ግጥም ውስጥ የተጠቀሱት ገጽ ባሕሪያት፣ ዲያብሎስ፣ ከነካዳሚዎቹ በሙሉ የፈጠራ ስሞች ናቸው። አንድ ሰው ግብረ ሥራው ከዚህ ግጥም ጋር ቢመሳሰልብት፣ የራሱ ጉዳይ ነው። ደራሲው በአፈላማ ላይያዝ፣ በአፍ እላፊ ላይከሰስ መብቱን የተጠበቀ ነው።

---

[3] ኤፌሶን 6 ቁ. 11-17
[4] ተሰሎንቄ ፭ ቁ. 8